# <u>አወቅኩ ያለ ጣጣ ያመጣል</u>

ደምሴ አሰግድ አሻግሬ

በቅርቡ ፕሮፌሰር ዓለማየሁ ገብረ ማርያም የተባሉ ሰው በእንግሊዝኛ ባቀረቡት ፅሁፍ የደርግ ሸንጎ አባል የነበሩትን ዶክተር ኃይሉ አርአያን በአርበኝነትና ቆራጥ ታጋይነት በኃለ መንፈስ አወድሰዋል፡፡ ዳጉሳ ዳቦ ሆነና ነገሩ ምነው ገና ሳንሞት ወይም የዘመኑ አንጎል አሳቹ አልዝሃይመ ር በሽታ ሳይዘን ይህ ዓይነት አጓጉል ታሪክ ይቀርባል በሚል ይህን ፅሁፍ ማቅረብ ተገደድኩ፡፡

ፕሮፌሰር አለማየሁ ዶክተር ኃይሉ አርአያን ጠንቅቀው የሚያውቁ አልመሰለኝም፡፡ እኔ ግን ዶክተሩን በዚያ በጨለማ ዘመን ለመንግስቱ ኃይለማርያም አጋር ሆነው ሳሉ አውቃቸዋለሁ፡፡ ወደ ግል ታሪክ ዝርዝር በዚህ መግባቱን ልተወው እንጂ ከደርጉ መሪ ከፍስሐ ደስታም ጋር በማያያዝ ብዙ የሚተረክ ባልጠፋም ነበር፡፡ ይህን አጓጉል ግምገማ ያቀረቡት ራሳቸው ፕሮፌሰር አለማየሁም ቢሆኑ አጠያያቂ ሰው መሆናቸው በሌሎች በየጊዜወ የተተቸ ስለሆነ ብ.ዙ የምለው የለኝም፡፡ ፕሮፌሰሩ ነጋ ጠባ በእንግሊዝኛ ትችት ያቀርባሉ፤ ይራቀቃሉ፡፡ በፖለቲካው ዓለም ብዙ ሚና የነበራቸውና ተመክሮ የገበዩ ባይሆኑም ሁሉንም አስተማሪና አራቂ ነኝ ብለው መነሳታቸው የሚታይ ነው፡፡ በአንድ ወቅት አለማየሁ የሚለውን ስም ትተው ራሳቸውን አል ብለው ነበር፡፡ በአሜሪካንኛ  ሳይሆን በእኛው ቋንቋ ከወሰድነው “ አል ” አፍራሽ ነው፡፡ አልሄደም፤አልበላም፤ አልተኛም፤ አልወቀሰም፤አልገባውም፤አልነቃም፤ አልተማረም፤ አልገበየም ወዘተ..አል ማርያም እንግዲህ ትርጉሙ ምን ይሆን? ይኼን በዚሁ በፈገግታ ደረጃ እንተወውና ወደ ፕሮፌሰሩ ነጋ ጠባ ንግግሮችና ፅሁፎች ስንገባ ደግሞ የሐማሴን ዱቄት እንዳደረግከው ይሆናል የሚለውን የትግሪኛ ተረት ያስታውሳል፡፡ ቅፅል ሞልቷል፡፡ ለሚወዷቸው የፖለቲካ ሰዎች የሚሰጡት ምስጋ ናና አድናቆት መረን የለሽ ነው፡፡ የሚጠሏቸውን ደግሞ ያክቾለችላሉ፤ከመድረክ ይወገዱ ይላሉ፡፡ ዶከተር ኃይሉ ዘደርግን የሚያደንቁት ፕሮፌሰር እንዴት ሌሎችን ይተቻሉ ለሚለው ጥያቄ ሊሰጥ የሚችለው መልስ ምስጢር ሊሆን አይችልም፡፡ ፕሮፌሰር  አለማየሁ ከየትኛው የፖለቲካ ጉድጓድ ብቅ ብለው ዛሬ መድረኩን ያዙ ብሎ መጠየቅም የግድ ይሆናል፡፡

ዶክተር ኃይሉ አርአያን አርበኛ ና አርአያ ሊሉን ሞክረዋል፡፡ በመንግስቱ ኃ.ማ. የመጨረሻ ሰዓታት በሸንጎ የተናገሩትን መሰረት በማድረግ፡፡ መርከብ ሊሰምጥ ሲል አይጦችም ወደ ባህር ዘለው ይተዉታል የተባለውን ምዕራባውያን አባባል ያስታውሳል፡፡ የመንግሰቱ ሃይለማርያም መርማሪ ኮሚሽንና በለው በርታ አማካሪ የነበሩት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያምም ወደ መጨረሻው ዘመን የአዛውንት ሸንጎ የሚል ነገር አምጥተው ጆሮአችንን ሲጠልዙ አልነበሩምን? ዶክተር ኃይሉ አርአያ የደርግ አጋር ነበሩ ፤ በሸንጎ ሚናቸውም ሂሳዊ ድጋፍ ይባል በነበረው ዓይ ነት አልነበረም፡ስለዚህ ዶክተር ኃይሉን “አርአያ”  ማለቱ የአባታቸውን ስም ከመጥራት ሌላ ትር ጉም ሊኖረው አይችልም፡፡ ፕሮፌሰሩ ዶክተሩን አርበኛ ሲሉም ያግቦ ንግግር እስካልሆነ ድረስ

ስለ አርበኝነት ትርጉም ፕሮፌሰሩ ያላቸው ግንዛቤ ጨገሬታው የጠፋ ይሆናል (ባንዳዊ ነው ላለማ ለት) ። በወደቀ ዛፍ ላይ ምሳር በዛባት ሆኖ በመጨረሻው ጊዜ መንግስቱን ያልደፈረና ያልከዳስ ነበር? ዶክተርኃይሉ አርበኛ ሳይሆኑ አድርባይ ነበሩ። ልክ እንደ ፕሮፌሰር መስፍን። ወያኔ ኢሕ አዴግ ስልጣንን ሲይዝም ተስተካክለው እንደ ፕሮፌሰር መስፍን " ለነጭ ሽብር " ሰለባዎች ሀውልት ይሰራ ሲሉና በተለይም ፀረ ወያኔ የነበሩትን ድርጅቶች ሲወርፉ እንደነበር የሚታወቅ ነው። ምን ከልጓም ይጠቅሳል ዓይነት ክርክራቸውንም በነፃ ጋዜጦች በየጊዜው ሀገር ወዳዶች ተችተውባቸዋል። ፕሮፌሰር አለማየሁ የወይዘሪት ብርቱካን ድርጅት ደጋፊና አድናቂ መሆናቸ ውን ደግመውደጋግመው የገለፁ ናቸውና ምናልባትም የወይዘሪት ብርቱካን የድርጅት ረዳትና የስራ ባልደረባ የሆኑትን ዶክተር ኃይሉንም አርበኛ ማለታቸው ለዚሁ ይሆናል። ሀቅ ያልሆነ ነገር ሲፃፍ ግን ዝም ብሎ ማለፉ በተለይም በዘመነ ደርግ ገፈቱን ለቀመስነው የሚዋጥልን አይደለም።

ሀቁ ይነገር እያሉ ከሚጮኹት ኢትዮጵያውያን ጋር አብሬ መጮህ ፈላጊ ነኝ። ሲበድሉንና ሲጎዱን የነበሩት ወይም ከአምባገነኖች ጋር አብረው ሲደልቁ የነበሩ ዛሬ አርበኛ እየተባሉ፣አዋቂ እየተባሉ፣ታጋይ እየተባሉ ሲሞካሹ ዳግም በቁስላችን ላይ አሲድ መርጨት ይሆናል። እኚህ ፕሮፌሰር አለማየሁ ራሳቸው ማናቸው፣ ምነው አደብ አልገዛ አሉ፣ምነው በመጀመሪያ ታሪክን ቢማሩ፣ወዘተ ብለን መጠየቅ መገደዳችን አልቀረም። የእሳቸውን ባናወቅም እነ ዶክተር ኃይሉና ፕሮፌሰር መስፍንንና ሌሎችንም ግን በሚገባ እናውቃቸዋለን። እኛ ወዲህ እነሱ ከወዲያ ሆነው ስንፋለም። የታጋይ ደም ይጮኻል ተብሏል። ለዚህ ፕሮፌሰር አለማየሁ ጆሮ የላቸውም-- የወገኑት ከሌላ ሌላ ነውና። የታጋይ ደም ሲረጭ ደግሞ እነ ዶክተር ኃይሉና ፕሮፌሰር መስፍን ሱፍና የፓርቲ ልብሳቸው ላይ ተፈናጥቋል። ላውንደሪ አጣቢ ሊያፀዳው አልቻለም፣አይችልምም፡

ፕሮፌሰር አለማየሁ በሚሌኒየም የዋሽንግተን ስብሰባ አቡነ ዘዋይትሀውስ ሲያነበንቡና ለእነ ጆርጅ ቡሽ ምንጭር ቀራጭ ወይም ታማኝ ባለሟል ነኝ ሲሉ በጆሮዬ ሰምቻቸዋለሁ። ገራ ክንፍ ባሏቸው ላይ እንደ የቀድሞው ደርግ--ኢሠፓ ዶክተር መሳይ ሲዘምቱ ቆይተው በኦባማ ሰሞን ደግሞ ሌሎችን በቀኝ ክንፍነት ሲከሱ አንበናል። ዶክተር ኃይሉን አርበኛ ብለው ውዳሴ ማቅረባ ቸው መጠበቅ ያለበት ነው ቢባል ስህተት አይሆንም። ባይሆንም ስህተትን መጠቆም ደግሞ አስፈላጊ ነው። እንደ ዕወቅት ተድርጎ የተወሰደው የዘመኑ ፈሊጥ ብቅ ያለውን ጮሌ ሁሉ ማዳነቅ መሆኑን ያን ከህዲ ማንዴላ ሲሉ ያየነው የሰማነው ነው።ማጋነንና ሀሰት መርጨት ለየቅል ናቸው። የወያኔውን ቅጥረኛ ከማንዴላ ማወዳደሩ ሕዝብን አደናግሯል። ስዬ አብረሃንና ገብሩ አሥራትንስ አርበኛ ብለው ሊሸጡልን እየሞከሩ አይደለም?አርበኛ ያልነበረውንና ከአረመ ኔው የቀይ ሽብር ደርግ ጋር አብሮ የቆየውንም አርበኛ ማለት ወይ ከዚያው ጎራ በደም ተጫማል ቁ ነበር ብሎ ማመን ነው ወይም ደግሞ ሳያውቁና ባላወቁት ግግም ብሎ ዓይንን በጨው አጥቦ መፈትፈት፣ መቅጠፍ መዋሸት ነው።
ፕሮፌሰር ከመምከር በፊት ይመከሩ።